# የፊስቱላ ተጠቂዎች የተስፋ ታሪክ

**(በፊሱትላ በሽታና በዶክተር ካትሪን ተጋድሎ ዙሪያ ያጠነጠነ)**

መስፍን ማሞ ተሰማ - ሲድኒ አውስትራሊያ

## አዲስ አበባ ቤቴ

*"የሚያብረቀርቁ የቆርቆሮ ጣራዎችን ከበታቻችን ስንመለከት በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ እያንዣበብን መሆናችንን ተረዳን። አውሮፕላኑ ማሽቆልቆል ጀመረ። ያለ ምንም እንከንም ቆመ።... አቧራና ባህር ዛፍ የተቀላቀለበት የለመድነውን የአውስትራሊያ ምድር አየር ተነፈስን። እንደ አብዛኞቹ የአፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ሃገሮች ሁሉ ኢትዮጵያም ከአውስትራሊያ በመጡ የባሕር ዛፍ ፍሬዎች የተሞላች ነች። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው፦ ይህ የመጀመሪያው ስሜቴ ይሆን አዲስ አበባን ቤቴ እንድላት ያደረገኝ? እላለሁ... "*

ይላሉ ዶ/ር ካትሪን ሃምሊን፡ **"የተስፋ-ታሪክ - በወንዝ ዳር ያለ ሆስፒታል"** (A Story of Hope-The Hospital by the River) በሚለው መጽሃፋቸው።

ዶ/ር ካቲሪንና ዶ/ር ሬጅ ሃምሊን በአውስትራሊያ ሲድኒ ውስጥ ከሚገኙ ስመ ጥር ሆስፒታሎች በአንዱ ውስጥ በአዋላጅነትና በመሃጸን ስፔሻሊስትነት የሚያገለግሉ ሃኪሞች ነበሩ።

እ.አ.አ በ1957 **"ዘ ላንሰት"** በተባለው የእንግሊዝ ሜዲካል ጋዜጣ ላይ የወጣው ማስታወቂያ፦ **አዲስ አበባ ሚገኘው የልዕልት ፀሃይ መታሰቢያ ሆስፒታል ነርሶችን በአዋላጅነት የሚያሰለጥን ት/ቤት ለማቋቋም የማሕጸን ዶክተሮችን ለመቅጠር ይፈልጋል"** ይላል።

የሃኪሞች እጥረት ባለባቸው ሃገሮች ውስጥ የመስራት ፍላጎት የነበራቸው ሃምለኖች ማስታወቂያውን እንዳነበቡ ለቦታው አመልክቱ። በወቅቱ የነበረው የቀ.ኃ.ሥ መንግስትም ማመልከቻቸውን ተቀበለ፡፤

ዘመኑ እ.አ.አ 1957 ግንቦት ወር ነበር። ዶ/ር ካትሪንና ባለቤታቸው ዶ/ር ሬጅ ላን ሀምሊን የስድስት አመት ሕጻን ልጃቸውን ሪቻርድ ሀምሊንን ይዘው አዲስ አበባ ገቡ።

እንሆ ለሦስት አመት የፈረሙት የሥራ ኮንትራት ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ በማስቆጠር ላይ በሚገኘው የሕይወት ማዳን ተልዕኮ ተቀይሮ ይገኛል።

ዶ/ር ካትሪን ሀምለን በአሁን ሰአት የ86 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ናቸው።ጡረታ አልወጡም። ይሁንና በአውስትርሊያ ግዛት በአንድ የባህር ዳርቻ በሚገኘው ምቾታማና የናጠጠ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ቀሪውን የህይወት ዘመናቸውን እንኳ ለማሳለፍ አልፈለጉም።ዛሬም በዚህ እድሜያቸው ከሃገር ሃገር እየዞሩና እየተንከራተቱ ዕርዳታ በመጠየቅ የፊስቱላን በሽታ ከምድረ ኢትዮጵያ ለማስወገድ እንዲቻል የፋይናንስ፤ የማቴሪያልና የባለሙያ ኃይልን እያደራጁ ይገኛሉ።በፊስቱላ ሆስፒታሎች ኦፐራሲዮን በማድረግና በሌሎችም የአስተዳደር ስራዎች ተጠምደው ይጠመዳሉ።

*"አብዛኛውን እድሜዬን ያሣለፍኩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ሌላ ሃገር ኖሬ አላውቃም። ከ እንግዲህ ምን አልባት አንድ አመት ወይም አምስት አመት ልኖር እችል ይሆናል። እኔ ካለፍኩ በኋላ የጀመርነውን ሥራ ግቡን ሳይመታ እንዳታቆሙ አደራ! ፊስቱላን ከኢትዮጵያ ገጽ ማጥፋት አለብን፡፡"*

ዶ/ር ካትሪን ይህን ቃል የተናገሩት፤ በኦክቶበር 2009 በአውስትራሊያ ርዕሠ ከተማ ካንቤራ ውስጥ የሳቸውን የኢትዮጵያ ቆይታ ተመርኩዞ በተሰራውን ዶክመተሪ ፊልም የምረቃ ዝግጅት ላይ ነበር፡፤ በዝግጅቱ ቤተሰቦቻቸውና በተለይም ከዛሬ 50 በፊት በ6 ዓመቱ አብሯቸው ወደ ኢትዮጵያ የተጓዘው ልጃቸው ሪጃርድ ሀምለን ተገኝቶ ነበር።

ኢትዮጵያዊያኑ የፊስቱላ ህሙማን "አባታችን" ዕያሉ፤ የሚጠሯቸው፡- የዶክተር ካትሪን ባለቤት የሆኑትና ቀልድ አዋቂ፤ ራዕያቸው ከአድማስ የዘለቀ፤ ታታሪና በሙያቸው እጅግ የተካኑት ዶ/ር ሬጅ ሀምሊን ባደረባቸው ህመም ኦገስት 5 1993 (እ.አ.አ) በተወለዱ በ85 ዓመታቸው ሲያልፉ፤ አጽማቸው ያረፈው አዲስ አበባ ማህጽን ውስጥ ነው፡፤ኢትዮጵያ ቤታቸውም መቀበሪያቸውም ሆነች።

ዶ/ር ሬጅ ባለቤታቸውንና ሕጻኑን ልጃቸውን ይዘው በ1959 ወደ አዲስ አበባ ከማቅናታቸው ቀደም ብሎ የ6 ዓመቱን ሪቻርድን መጭ ህይወት አስመልክቶ ውሳኔ መስጠት ተቸግረው ነበር። እናም ጉዞው እየተቃረበ በነበረበት ሰሞን ታዳጊ ሕጻን ሪቻርድን ት/ቤት ካደረሱት በኋላ ረዥም መንገድ በመንዳት ጉዳዩን እያውጠነጠኑ ከአንድ ማረፊያ ሥፍራ ጎራ ይላሉ።

በአቅራቢያቸው ተቀምጦ ቢራ ይጠጣ የነበረ አውስትራሊያዊ "ምነው ጃል ? በጣም ሃሳብ የገባህ ትመስላለህ" ይላቻዋል። ዶ/ር ሬጅም በቅርቡ ከባለቤታቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ ሊሄዱ እንደሆነና የ6 ዓመት ልጃቸውን በተመለከተ ግን አብሯቸው ይሂድ ይቅር የሚለውን ለመወሰን እንዳልቻሉ ይነግሩታል።

ሰውየውም " **ኢትዮጵያ የተመለስኩት በቅርቡ ነው። ውብ የሆነች ሃገር ነት፡፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለካርታ ሥራ ተልዕኮ 3 ዓመት ቆይቻለሁ። ሃገሪቷን ወድጃታለሁ። ማለፊያ የእንግሊዘኛ ት/ቤት አለ። ልጄ የተማረው እዛ ነው፡፤ እዚህ ከመጣ በኋላም ጥሩ ት/ቤት ለማግኘት ምንም ችግር አላጋጠመውም ልጅህም በጣም ይወደዋልና ይዘህው ሂድ"** ብሎ የመከራቸዋል።

ዶ/ር ሬጅም እጅግ ደስተኛ ሆነው ህሊናቸውን ካስጨነቀው ሃሳብ ተገላግለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

በርግጥም ወጣቱ ሪቻርድ እንደወላጆቹ ሁሉ ኢትዮጵያን ወደደ። ኢትዮጵያን ቤቴ ብሎ መጥራት ጀመረ። ሪጃርድ ሃምለን እንግሊዝ አገር ለትምህርት ቆይቶ ወደ ኢትዮጵያ ለእረፍት የሚመለስበት ወቅት ሲቃረብ ለወላጆቹ በጻፈው ደብዳቤ፡-

*"እንሆ ወደ ገነቲቱ ምድር በሃሴት የምመለስበትን ቀን እየቆጠርኩ ነው። የ እድሜዬን አብላጫ ዘመን ከኖርኩበት፤ ከማንነቴ ጋር ከተቆራኙቺውና ከቶ ማንም ከኔ ሊነጥላት ከማይችሸለው ምድር የምመለስበት*

*ቀን እንደምን ያለ ጣፋጭና ማራኪ ይሆን? መቼም በደስታ አብዳለሁ። እናንተን፤ ውጮቻችንን፤ ሠራተኞቹን፤ ጓደኞቼን፤ ገጠሩን፤ ህዝቡን፤ ፈረሶቹን፤ግቢያንንና እጅግ ተወዳጇን አሮጌ ቤታችንን ሁሉ ዳግመኛ አያለሁ"* ብሏል።

አዎ ሪቻርድ ሀምሊን በዘመናዊቷ የሎንዶን ከተማ ሆኖ አዲስ አበባ ያለቺው የጭቃ ምርጊቷ አሮጌ የወለጆቹ ቤት ናፈቀችው።

## ፊትሱላ ፒልግሪምስ

የልብሳቸው አዳፋነት ከመሬቱ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሥጋቸው ከላያቸው ሟሾ አጥንታቸውን ብቻ ለመሸፈን የተለጠፈ ይመስላል። ሕይወት አልባ በሆነው ገጽታቸው ላይ ከአይኖቻቸው ዓይነ-ውኃ የዝንተ ዓለም ሰቆቃ፤ ሥቃይ፤ ውርደትና አዝጋሚ ጣረ ሞት ይታያሉ።

ለአያሌ አመታት ከሰው ዘር ተገልለው፤ ከማህበረሰቡ ርቀው፤ መንጋትና መምሸቱን እንኳ ማወቅ እስኪሳናቸው በብቸኝነት የኖሩ በመሆኑ እንደሰው ልጅ የመግባቢያ ቋንቋ እንዳላቸውም ረስተዋል፡፡ ለነሱ አዲስ አመት ትርጉም የለውም ። እነሱ ወልዶ መሳም አሳድጎ መዳር አልታደሉም። እነሱ ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን እግሮቻቸውን ተጠቅመው ገበያ አይወጡም፡፤ ሠርግ አይሄዱም።

እነሱ እንግጫ ነቅለው፤ አበባ አየሁ ወይ ብለው ፤ ቅልልቦሽ ተጫውተው ሣይተግቡ በልጅነት ለጋ ሰውነታቸው ለጎረምሳ ተድረው፤ በልጅ ማሕጸናቸው ልጅ አዝለው፤ ልጅ አምጠው፤ ...አምጠው..ሕይወት አልባ ሕጻን ወልደው ውስጠ ውስጣቸው ከአካልነት ተራ ወጥቶ ህይወታቸው ከቆሙት በታች ከሞቱት በላይ የሆነባቸው ኢትዮጵያዊያን የፊስቱላ ሰለባዎች ናቸው።

ፊስቱላ ሴቶችን ለዕድሜ ልክ ውርደትና ድኩምነት የሚዳርግ በምጥ ሳቢያ በሽንትና በመጸዳጃ መቆጣጠሪያ ላይ ዘላቂ ችግር የሚያስከትል ዘግናኝ በሽታ ነው።

በመሆኑም የፊሱትላ ተጠቂዎች ሽንትና ሌላውንም መቆጣጠር ባለመቻላቸው ምክንያት ከህብረተሰቡና ከወዳጅ ዘመድ ርቀው ለብቻቸው ኖረው፤ ልብቻቸው አልቅሰው፤ ለብቻቸው ማቀው፤...ብቻቸውን ክልትው ይላሉ። የዘላለም እንቅልፍ ያንቀላፋሉ።

በሕይወት የሚገኙትም፤ ከወደ አዲስ አበባ የተሰፋ ጮራ መፈንጠቅ መጀመሩን ሲሰሙ፤ በበቅሎ፤ በአህያ፤ በሰው-ጀርባና በሚገፋ ጋሪ እየተጫኑ ለሣምንታትና ለወራት በመጓዝ ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ወደ አዲስ አበባ ይተማሉ።

አቀበት ወጥተው ቁልቁለት ወርደው፤ ክፍለ ሃገራትን አቋርጠው ትንሣኤ ህይወት ለማግኘት የሚመጡትን የፊስቱላ ተጠቂዎች ዶ/ር ሬጅ ሀምሊን "ፊስቱላ ፒልግሪምስ" ይሏቸዋል። ከጉዟቸው ርዝመት ከእንግልትና ከድካማቸው ።

ተስፋ በጠፋበት ምድረ-በዳ ተስፋ ላገኙ፤ ህይወት በጨለመበት ሸንተረርና ሸለቆ፤ ቁጥቋጦና ጋራ የሕይወትን ሻማ ብርሃን ማየት ለጀመሩ የፊስቱላ ህሙማን ...ፊስቱላ ፒልግሬምስ እንደምን ያለ ዕጹብ መግለጫ ነው።

የሕክምናው ጥበብ ከማደጉና የአዋላጅ ሙያተኞች ቁጥር ከመብዛቱ በፊት (1800 መገባደጃ ዓመታት ድርስ) ዛሬ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት የሚታየው የፊስቱላ በሽታ በአውሮፓና በአሜሪካም የተስፋፋ ነበር።

እንሆ ፊስቱላ ባደጉ ሃገራት ውስጥ ከጠፋ ዘመናትን አስቆጥሯል።የአንድ ሃገር እድገት መለኪያ ከሆኑ ተቋማት አንዱ የህክምና አገልግሎት ለዜጎች በብቃትና በጥራት መድረስ መቻሉ ነው።በዚህ ረገድ የአደጉት ሃገራት እናቶች ምጥን ተከትሎ የሚከሰተው አሰቃቂው የፊስቱላ በሽታ መዘዝ የለባቸውም በመሆኑም የምዕራቡ ዓለም ዶክተሮች ፊስቱላን "ከቴክስት ቡክ" (የትምህርት መጽሃፍ) ውጭ በተግባር አያውቁትም።

ስለሆነም ሀምለኖች ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ የፊስቱላ ተጠቂዎች ሲያጋጥሟቸው አያሌ ፈተናም ነበር የገጠማቸው። የህክምና አግልግሎት ገና መዳህ እንኳ ባልጀመረበት በዛን ዘመኒቷ ኢትዮጵያ፤ የምርምር መጽሃፍት፤ የሣይንስ ጆርናል፤ እና ተጓዳኝ ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ከቶም የማይታሰብ በመሆኑ ሁለቱ ባልና ሚስት ከውጭው አለም ጋር መጻጻፍና ማቴሪያል ማሰባሰብ፤ ማጥናትና ከተጨባጩ ችግር አንጻር ህክምናዊ ዘዴና ጥበብን መፍጠር ነበረባቸው፡፤

እናት ካትሪን ስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፉ "

> *ያሰባሰብናቸውን መረጃዎች በሙሉ ካነከናቸው በኋላ የመጀመሪያውን ፊስቱላ ለመጋፈጥ ብቃት እንዳለን ተሰማን። ለዚህም የመረጥናት ከገጠሪቷ ኢትዮጵያ የመጣችና የሽንት መቆጣጠሪያዋ በመጠኑ የተቀደደ ቀለል ያለ ችግር(ኬዝ) የነበራትን ወጣት ነበር፡፤ ሬጅ ኦፕሬሽኑን ሲያካሂድ እኔ ረዳቱ ነበርኩ። ከዚህ በኋላ ይህቺን መንፈሰ ብርቱ፤ ርጋታ የተላበሰችና፤ እራሷን አሳልፋ የሰጠችንን ወጣት አስተኝተን እጅግ አስጨናቂውንና አዝጋሚ የሆነብንን የማገገሚያ ቀናት መቁጠር ጀመርን።ከ14 ቀናት በኋላ ልጅቱ እንደማንኛው ጤነኛ ሰው መሽናት ቻለች። እጅግ ደስታ ስለተሰማንም ወደ መጣችበት ቅዬ ከመመለሷ በፊት ከሬጅ ጋር ፎቶ እንድትነሳ አደረግን አዲሱን ሕይወቷን ለመጀመር ከመጓዟ በፊት እጃችንን ስማ ያመሰገነችንን እስከመቼም አልረሳውም፡፤ እሷን ማዳን መቻላችን ለኛ ዘላቂ ሥራ የመሰረት ድንጋይ መሆኑን ግን አታውቅም ነበር።ከዚህ በኋላ ሁለት የፊስቱላ ተጠቂዎችን ቀዶ ህክምና አደረግናላቸው፤ ሁለቱም ሙሉ ለሙሉ ዳኑ"* ሲሉ ገልጸዋል።

እንሆ ሃምለኖች ለ50 ዓመታት የዘለቀውን የህይወት አድን ተልዕኮ የጀመሩት በዚህ መልክ ነበር።

በልዕት ጻሃይ ሆስፒታል ለህክምና የሚመጡት የፊስቱላ ተጠቂዎች ወደ ሆስፒታሉ ሲመጡ ከቁጥጥራቸው ውጭ በሆነው የመጸዳጃ አካሎቻቸው በሚወጡ ፈሳሾች ሰውነታቸውና ልብሶቻቸው የተበከሉና ልዩ ጠረን ያላቸው በመሆኑ የሚቀርባቸው አልነበረም።

ዶ/ር ሬጅና ዶ/ር ካትሪን ሌሎች ሊቀርቧቸው የተጠየፏቸውን ህሙማን በመቅረብና እጃቻቸውን ከተከሻቸው ላይ በማሳረፍ እያበረታቱ **"ዛሬ ለኔ ከሁሉም የላቅሽ በሽተኛ አንቺ ነሽ፡፤ ከሁሉም በፊት የማከመው አንቺነው በማለት"** ተስፋቸውን ያለመልሙላቸው ነበር።

ከዘመድ አዝማድ ጀምሮ አገር ምድሩ ከሩቅ የሚሸሻቸው ህሙማን እንዲህ ያለ ሰባዊ ርህራሄ፤ፍቅርና አክብሮት ሲቸራቸው ሃምሊኖቸን ከናት አባትም በላይ እንደ ጻድቃን፤ አልያም እንደ መላዕክት ቢያይዋቸው ይበዛባቸው ይሆን?

በአንድ ወቅት "ኒዮርክ ታይምስ" በዘገባው "ዶ/ር ካትሪን ሀምለን የዘመናችን አዲሲቷ ማሪያ ቴሬዛ ናቸው" ሲል አድናቆቱን ቸሯል።

ታዋቂው አውስትራሊያዊ የቴሌቪዥን ሰውና ጸሃፊ፤ ጆን ሊትል፤ "የካትሪን ስጦታ"(ካትሪንስ ጊፍት) ጥልቅና ብስል መጽሃፉ ውስጥ ከገለጻቸው አያሌ የፊስቱላ ህሙማን መካከል ለአብነት ያህል ጥቂቱን እንሆ፡-…

**<u>አሚና</u>**
አሚና መሀመድ 20 ዓመቷ ነው። እንደ ኑግ የሚያብረቀርቅ ቆዳ፤ የተዋጣለት ተክለ ቁመና፤ የጎሉና ንቃት የተሞላቸው አይኖች ያሏት ውበቷ ልብን የሚሰርቅ ነው።

አሚና በምዕራቡ ዓለም ብትኖር ኖሮ ዓለምን በእግሮቿ ሥር ማድረግ በቻለች ነበር። ነገር ግን የሕይወቷ እጣ-ፈንታ የተወሰነው ገና ከጥዋቱ ነበር። ጋብቻ፤ ሥራ፤ ሞት። እናትነት ለሷ ከምንም በላይ ነው፡፤ እናት መሆን ካልቻለች-ምንም አይደለችም።

በ14 ዓመቷ ለጋብቻ ዝግጁ ነች ተባለ።በ15 ዓመቷ ተዳረች።ልጅነቷ አከተመ። ከ3 አመት በኋም አረገዘች…3ማዕልትና 3 ሌሊት አማጠች…ህይወት አልባ ሕጻን ወለደች። ለአሰቃቂው ፊስቱላ ተዳረገች።

**<u>ወርቅነሽ</u>**
ለግላጋና ቀጠን ያለች ወጣት ወደ ክፍሉ ገባች።የካትሪን ፊትም በደስታ በራ፤ "ነይ አጠገቤ የኔ ቆንጆ" አለቻት ሃሴት በተሞላው ፈገግታም አቀፈቻት ።አስተዋወቀችን።ወርቅነሽ ትባላለች። ለካትሪን ቅርብ ከሆኑት ወጣቶች መካከል አንዷ ወርቅነሽ ነች። አደገኛ በሆነ ተደራራቢ ፊስቱላ ተመርዛ ወደ ሆስፒታሉ ስትገባ አስራ ስምንት አመቷ ነበር።

"እዚህ ስትመጣ አጽም ነበረች፤ ከሙታን መንደር ነው የተነሣቺው፤፡" አለችን ካትሪን በትውስታ ወኋላ ተመልሳ።

ወርቅነሽ ከነበረችበት ዘግናኝ ሁኔታ ለማውጣትና ሙሉ ለሙሉ ለማዳን አስራ ስምንት ወራት ፈጅቷል። ወርቅነሽ ወደ መጣችበት ቅዬ ከመመለስ ይልቅ ረዳት ነርስ ለመሆን ነበር ካትሪንን የጠየቀቻት።

"አሁን የተዋጣለት ነርስ ነች። ስለ ሆስፒታሉ ስላሉት ህሙማን ሁሉንም ጠንቅቃ ታውቃለች። " አለችን ካትሪን የናትነት ኩራት ባልተለየው መንፈስ፡.."

__ማሚት__

"እሺ ማሚት ለመሆኑ አሁን እዚህ ስንት ዶክተሮች አሉ? " አልኳት ጠንካራውን ጥቁር ቡና እየሳብኩ፤ በጣቶቿ መቁጠር ጀመረች። ዶ/ር አምባዬ፤ ዶ/ር ሙሉ ፤ዶ/ር ይፍሩ ፤ ዶ/ር ብሩክ፤ እና እናት-" አለችኝ፡፤ በተጨማሪም አንቺ አልኳት፤

" እረ በፍጹም እኔ ዶክተር አይደለሁም " አለቺኝ

ማንበብና መጻፍ የማታውቀው ማሚቱ ጋሼ፤ በሞት አፋፍ ላይ ሆና ወደ ልዕልት ጸሃይ መታሰቢያ ሆስፒታል የመጣቺው እ.አ.አ በ1962 ዓ.ም የ16 ዓመት ለጋ ሆና ነበር።

ለአራት ቀናት በዘለቀው ምጥ ሳቢያ በውስጥ አካሏ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። ሙያዊ ብቃት የሌለው የመንደር ወጌሻ በውስጧ የሞተውን ሕፃን በጉልበት መንጥቆና ባረጀ ቢላ ቆርጦ ካወጣላት በኋላ ለተጨማሪ ዘግናኝ ቁስል ዳረጋት።

ለበርካታ ተከታታይ አመታት በርካታ ቀዶ ጥገናዎች ተደርገውላታል። ሆኖም የደረሰባት ጉዳት ከባድ በመሆኑ ምክንያት ማሚቱን ሙሉ ለሙሉ ማዳን አልተቻለም። ማሚቱ እነደ ማንኛው ጤነኛ ሴት ወደ ቅዬዋ ተመልሳ ሠላማዊ ኑሮ መኖር አትችልም።

በመሆኑም ሃምሊኖች በሆስፒታሉ ውስጥ መኖሪያና ሥራ ሰጧት። ማሚቱ ብሩህ አይምሮና ከፍተኛ ተስዕጦ ያላት በመሆኑ ቀስ በቀስ ዶ/ር ካትሪንን ከመርዳት አልፋ በቀጥታ በቀዶ ህክምና ሥራ ውስጥ መሳትፍ ጀመረች። እንሆ ማሚቱ ዛሬ በሙያው በእጅጉ የተካነች የቀዶ ህክምና ሃኪም(ሰርጀን) ሆናለች።

"የማሚቱ ጉዳይ የሚገርም ነው ። የተለመደው መንገድ መጀመሪያ ት/ቤት መግባት፤ከዚያም ዩንቨርሲቲ ቀጥሎም በዓለም የተደነቁ(ቀዳጅ ሃኪም)መሆን ነው። ማሚቱ ግን እያደረገች ያለቺው የተገላቢጦሽ ነው።" ይላል ጆን ሊትል በመጸሃፉ።

እናት ዶ/ር ካትሪንም ሲጽፉ "ማሚት የተማረች ብትሆንና መደበኛ የህክምና ትምህርት ቢኖራት ያለምንም ጥርጥር በየትኛውም አለም መስራት የምትችል ሥሙ-ጥር ጥር ሰርጀን መሆን ትችል ነበር፡፤ ይሁንና እንደ ማሚቱ ዓይነት ታሪክ ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ በርካቶች አሉ።" ብለዋል፡፤

* * *

በዓለም ዙሪያ ሁለት ሚሊዮን የፊስቱላ ህሙማን ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ ሁለት መቶ ሺዎቹ የሚገኙት በኢትዮጵያ ነው፡፤ ይህ ቀላል ግምት የሚሠጠው ቁጥር አይደለም። በዓለም ላይ ካሉት ህሙማን 10 በመቶው የሚገኙት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ማለት ነው።

የአላማና የመንፈስ ጽናት ያላቸው ሃምሊኖች ከምንም ተነስተው በከፈሉት ወደር የሌለው መስዋእትነት ዛሬ ከ35 ሺህ ባላይ ሴቶች ወገኖቻችን ከዚህ ዘግናኝ ህመም ተፈውሰው ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለዋል።

ያም ሆኖ አሁንም በፌስቱላ በሽታ ሳቢያ ህይወታቸው በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የሚገኝ ከ150 ሺህ በላይ ሴቶች ወገኖቻችን በኢትዮጵያ የተለያዩ የገጠር ክልሎች ይገኛሉ።

ከነኚህ ውስጥ ምን ያህል አሚናዎች፤ ምን ያህል ወርቅነሾች፤ ምን ያህል ማሚቱዎች ይገኙ ይሆን?

## ደስታ መንደር

ወደ ፊስቱላ ሆስፒታል ከሚመጡት ህሙማን መካከል ስምንት በመቶ የሚሆኑት የደረሰባቸው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ድነው ከህብረተሰቡ ጋር ለመቀላቀልና ሠላማዊ የዕለት ተለት ኑሮ ለመቀጠል አይችሉም።አንዳንዶቹ የሽንት መቆጣጠሪያቸው ሙሉ ለሙሉ ከአግልግለአት ውጭ ሆኗል። ወይም የቁስሉ ደረጃ በቀዶ ህክምና መዳን የማይችል ሆኗል።

በመሆኑም እነኚህ ህሙማን ፈሳሻቸውን የሚያጠራቅሙበት የተለየ የህክምና ላስቲክ እድሜ ልካቸውን እንዲኖራቸው ግድ ይላል። እነኚህ ህሙማን የባለሙያዎችን የቅርብ ክትትል ይሻሉ። የአካልም የመንፈስም ጉዳተኞች በመሆናቸው ከፍተኛ እንክብካቤ በሚያገኙበት ስፍራ መኖር አለባቸው።

ለዚህም ነው እናት ዶ/ር ካትሪን "ደስታ መንደርን" የመሰረቱት። ደስታ መንደር ከአ/አ የአንድ ሰአት የጉዞ ርቀት ላይ የሚገኝ ሠላማዊና ርጋታ የሰፈነበት፤ እጅግ በጣም የጸዳና በአበቦች መዓዛ የታወደ መንደር ነው። በክብ ቅርጽ የተሠሩ መስህብ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ባሉት በዚህ መንደር የሚኖሩት የፊስቱላ ህሙማን በልብስ ስፌት፤ የእጅ ጥበብና፤ በጓሮ አትክልት ሙያ ሰልጥነው አምራች ዜጋም በመሆን ህመማቸውን የሚረሱበት ድንቅ እንቅስቃሴ ያደረጋሉ።

ከደስታ መንደር ነዋሪ ህሙማን መካከል አንዷ አጀቡሽ ናት።**አጀቡሽ** የተገኘቺው ከመቱ አካባቢ ነው። አንዲት መስኮት ባላት ጠባብ ክፍል ለዘጠኝ አመት ያህል ብቻዋን ተኮራምታ ስትተኛ፤ በዛቺው መስኮት ምግብ ከምታቀብላት እህቷ በስተቀር የሰው ዘርና ብርሃን ሳታይ ኖራለች።አጀቡሽ ለዓመታት የተኛችበት የጎን አጥንቷ ከአገልግሎት ውጭ የሆነ በ15 ዓመቷ ለፊስቱላ የተጋለጠች ወጣት ነች።

አጀቡሽን በእግሯ ለማቆምና ለማንቀሳቀስ 3 አመት ፈጅቷል። ለዘጠኝ አመታትም አንደበቷ ተዘግቶ በብቸኝነት በመኖሯ ቃላትን አውጥቶ ለመናገር ከፍተኛ ችግር ገጥሟት ነበር።

ዛሬ አጀቡሽ ደስታ መንደር ውስጥ ከሚኖሩት ኮኮብ ወጣቶች አንዷ ነች። ብሩህ አይምሮ ያላት በመሆኑም የሁለተኛ ክፍል ትምህርቷን ያጠናቀቀቺው በአንደኝነት ነው። ደስታ መንደር ውስጥ በመዝገብ ያዥነት ተቀጥረው ከሚሰሩት በላይ የመዝገብ አያያዝ ችሎታዋ ከፍተኛ ነው። በቅርቡም ኃላፊነቱን ወስዳ እየሰራች ትገኛለች።

የአጀቡሽን ታሪክ ስናነብ ሌሎች አጀቡሾች ፣ ሌሎች አሚናዎች፤ ሌሎች ወርቅነሾች ና ሌሎች ማሚቱዎች በእዝነ ልቦናችን ሲታሰቡን ግድ ነው።

የፊስቱላ በሽታ ሠለባ የሆኑ እህቶቻችን የመንፈስ ጽናታቸውና የአይምሯቸው ብሩሁነት ቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት በላይ ነው። ደስታ መንደር ውስጥ ውስጥ አንድን በሽተኛ መግቦ አልብሶና ሌሎች መሰረታዊ ነገሮችን አሟልቶ ለማኖር በአመት ከ33-34 ሺህ ብር ያስፈልጋል። ይህ በአውስትራሊያ ዶላር ሲሰላ 4000 ዶላር ይሆናል።

በፊስቱላ የሚታከሙት ተጠቂዎች እየተበራከቱ በሄዱ ቁጥር ወደ ደስታ መንደር መምጣት ያለባቸው ህሙማንም ቁጥር በዛው መጠን እየጨመረ ነው።በቅርቡም የደስታ መንደር እንደሚሞላ ይጠበቃል። ይህም እናት ዶ/ር ካትሪንና የፍስቱላ ፋውንዴሽን ሃላፊዎችን በእጅጉ እያስጨነቀ ነው።

## ለመሆኑ ወጪው የሚሸፈነው እንዴትና በማን ነው?

"ኤ ስቶሪ ኦፍ ሆፐ ዘሆስፒታል ባይ ዘ ሪቨር" የተሰኘው የዶክተር ካትሪን መጽሃፍ በ2004 በታዋቂዋ አሜሪካዊት የቴሌቪዥን ንግስት ኦፕራ ዊንፍሪ ፕሮግራም ላይ ከተዋወቀና በኋላ ዶ/ር ካትሪ በፖሮግራሙ ቀረቡ:: ኦፕራም **"ለመሆኑ ወጪው እንዴት ነው የሚሸፈነው ብላ ጠየቀች፡"** ዶክተር ካትሪንም ሲመልሱ "እንለምናለን። እኔና ባለቤቴ ሁሌም እኛ የተዋጣልን ፕሮፌሽናል ለማኞች ነን ነው የምነለው " አሉ። ምድር በያዘ የተረጋ አንደበት፡፤(በነገራችን ላይ የኦፕራ ውንፍሪ ሾው በአሜሪካ 97 ሚሊዮን በተለያዩ 117 ሃገራት ደግሞ በሚልዮን የሚቆጠሩ ታዳሚዎች ያሉት ፕሮግራም ነው።)

ቀደም ሲል ስለ ፊስቱላ ህሙማን በቀረበ ዶክመንተሪና በዶክተር ካትሪን ገለጻ በእንባ ሲታጠቡ የቆዩት የፕሮግራሙ እድምተኞች አንጀታቸው ተላወሰ። እንሆ ከዚያ በኋላ እናት ካትሪን እርዳታ ሊጠይቁ በሚዘዋወሩበት ሃገራት ሁሉ የረድኤት ድርጅቶችና ለጋሽ ግለሰቦች ያልተቆጠበ ርድታ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በአውስትራሊያ በተለያዩ ግዚያት በትረ-መንግስቱን የጨበጡት የሌበርና የሊብራል ፓርቲ መሪዎች የዶ/ር ካትሪንና የባለቤታቸውን የዶ/ር ሬጅን "ከኢትዮጵያ ምድር ፊስቱላን የማጥፋት ተልዕኮ " በቅርብ በመከታተል እርዳታ ሲያደርጉ ቆይተዋል።አሁንም እየረዱ ይገኛሉ።

ለፊስቱላ ተጠቂ ወገኖቻችን ፈውስ በመደረግ ላይ ካለው ርብርብ ሁሉ ፤ ምናልባት የኛን የኢትዮጵያውያንን ህሊና የሚመታና ውስጣችንን ዘልቆ እንዲሰማን የሚያደርገው የግብረ ሠናይ ተልዕኮ የሚከተለው ይሆን?

በአውስትራሊያ ሲድኒ የሚገኘው "አቦስትሊ" የሴቶች ት/ቤት በየአመቱ ሠባዊ ርዳታዎችን ለማድረግ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ያወጣል።

በ2004 የት/ቤቱ ሰባዊ ተግባር ፕሮጀክት በኢትዮጵያ የሚገኘው የፊስቱላ ሆስፒታል ላይ የተመሰረተ ነበር። ዘመቻውን "ፍቅር ለኢትዮጵያ" (To Ethiopia With Love) ሲሉ የሰየሙት 3

ግልከሰቦች ነበሩ።የፍስቱላን በሽታ አስከፊነት ማስተዋወቅ፤ የገንዘብ ዕርዳታ ማሰባሰብ፤ ሌሎችም ተጓዳኝ ተግባራዊ ሥራዎችን ማከናወን።

ቀጥሎም "የኢትዮጵያ በዓል ቀን" (Ethiopian Carnival Day) አዘጋጁ።በእለቱም ስለ ፊስቱላ አስከፊነት ሲያስተዋውቁ ዋሉ። እነኚህ ወጣቶች ለአንድ አመት በዘለቀው በዚሁ ተልዕኳቸው 23ሺህ ዶላር አሰባሰቡ፡፤ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ፕሮጀክታቸውም ልዩ ልዩ ህብረ ቀለማት ያላቸው 85 የአንገት ልብሶች ራሳቸው ሰሩ። የሰበሰቡትን ገንዘብና የሰሩትን የአንገት ልብስ ወደ ለፊስቱላ ሠላባዎች ከፍቅር መልዕክት ጋር ላኩ።

ዛሬ የአ/አ ፊስቱላ ሆስፒታልን የጎበኘ ሁሉ እነኚህን ባለ ህብረ ቀለማት የአንገት ልብሶች ያያል። በነኚህ የሲድኒ ወጣት ሴት ተማሪዎች የተፈጸመውን ሰባዊ ተግባር ስናስብ ህሊናችን አስገድዶን እራሳችንን እንድንጠይቅ መገደዳችን አይቀሬ ነው።

## እኛስ ምን ማድረግ አለብን?

ድህነትና ጎዋላ ቀርነት ከ300 ዘመናት በላይ ድንኳናቸውን አንሰራፍተው በዘረጉባት፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የነገ ሃገር ተረካቢ ሕጻናት ጎዳና በወደቁባት፤ በሽታዎች ሁሉ መናሐሪያ ባደረጓት፤ አረጋዊያን ጧሪ ቀባሪ ባጡባት፤ ሥራ አጥነትና ልመና መረን በለቀቁባት፤ ኢትዮጵያ ሃገራችን የቱን አንስተን የቱን እንደምንጥል ቢቸግረንና ተስፋ ቢስነት ቢጠናወተን፤ ጨለምተኝነትት ጡት ቢጣባን ይፈረድብን ይሆን?

ይሁንና ዘመናትን ያስቆጠረው ብሂል **"ሕይወት ባለበት ሁሉ ተስፋ አለ"** ይለናል። የተስፋ ታሪክም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው።

ተስፋ ቢስነት ላያሸመደምደን  የተስፋይቱ ምድር ዜጎች የተስፋ ታሪክ በውስጣችን አዲስ ተስፋን ያንሰራራል።የሁለቱ ሃሚሊኖች ፀረ-ፊስቱላ ትንንቅ ገድልና ድል የኛም ገድልና ድል ይሆን ዘንድ የተስፋ ታሪካችን በውስጣችን አዲስ የተስፋ ርችት ይለኩሳል። እናም እንደ ግለሰብ  በግለሰብነት እንደ ማህበረሰብ በሕዝብነት እንደ ዜጋ በዜግነት ለነኚህ ወገኖቻችን ምን ማድረግ እንችላለን? ብለን እራሳችንን እንጠይቃለን!!

የምላሻችንም መነሻና መድረሻ እኛውና እኛው ብቻ እንድንሆን ካድረግን (የፕሬዘዳንት አባን መሪ ቃል መድገም ባይሆንብን) አዎን እኛም ለውጥ ማምጣት እንችላለን። (Yes We Can Change)የሚል ይሆናል። በዚሁ ላይ በመመርኮዝም **እንችላለን** ለሚለው መሪ ቃላችን ገቢራዊነት እንሆ የሚከተሉትን ሁለት ንድፈ ሃሳቦች(proposals) እናቀርባለን።

## ንድፈ ሃሳብ አንድ

በምድረ ኢትዮጵያ በሃሚሊኖች ፋና ወጊነት በፊስቱላ ላይ በታወጀው የከተተ አዋጅ ባለፉት 50 አመታት ውስጥ ስለተደረጉ ተጋድሎዎችና ስለተገኙም ድሎች በስፋትና በጥልቀት የሚያትቱ ሁለት ታላላቅ መጽሃፍት በገበያ ላይ ይገኛሉ።

- (A Story of Hope-The Hospital by the River) በዶክተር ካትሪን
- (Catherine's Gift ) በጆን ሊትል ናቸው፡፤

ሁለቱን መጽሃፍት ለመግዛት የሚጠይቀን የገንዘብ መጠን ከነመላኪያው ከ100 የአሜሪካን ዶላር በታች ነው። ይህ ገንዘብ መጠን የዕለት ተዕለት ኑሯችንን የሚያንገጫግጭብን ወይም በፈረንጁ ዓለም የብድር ማሣ ውስጥ ለምንማስን ለተተጨማሪ ብድር የሚዳርገን አይደለም። ይሁንና ከሁለቱም መጽሃፍት ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ሙሉ ለሙሉ የሚውለው ለፊስቱላ ፋውንዴሽን በመሆኑ የኢትዮጵያውያን እህቶቻችንን ሕይወት በመታደግ ረገድ የሚኖረው አስተዋጾ ቀላል አይደለም።

እንሆ በአለም ዙሪያ ተበትነን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እስከ 7 ሚሊዮን ይገመታል። እንግዲህ በዚህ ስሌት መስረት ጥቂት መቶ ሽዎቻችን እንኳ እነኚህን መጽሃፍት እጃችን ብናስገባ፤ አልያም ለወዳጅ ዘመድ በስጦታ ብናበረክት፤ ለፊስቱላ ፋውንዴሽን ህይወት አድን ተግባር በሚልዩን የሚቆጠር ዶላር ልናስገባ እንችላለን ። በመሆኑም በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ የራሳችንንም ዕውቀት አዳብረን ወገኖቻችንንም የመርዳት ሰባዊ ተግባር ተሳታፊ እንሆን ዘንድ ይህን ንድፈ ሃሳብ አቅርበናል።

ይህን ማድረግ ማለት፤ በዋናነት በሺዎች የሚቆጠሩ እህቶቻችንን ህይወት መታደግ ማለት ሲሆን፡- በተጨማሪም ለ50 አመታት ርዳታ ፍለጋ በመንከራተት ላይ የነበሩትን(ያሉትን) እናታችንንም በመጨረሻ የዕድሜ ዘመናቸው እንኳ የጥረታቸውን ቀጣይነትን ተስፋ አይተው፤ በመጠኑም ቢሆን ሸክማቸውን ለማቅለል መነሳታችንን ተገንዘበው ቃላት ሊገልጹት የማይችሉት እፎይታ ያገኙ ዘንድ ማድረግ እንችላለን።ተስፋ ላጡ እህቶቻችን የተስፋ ብርሃን በመስጠት ላይ ላሉት እናት ካትሪን አጋዥ ተስፋ እንሆናቸው ዘንድ ህሊናችን ይርዳን።

### ንድፈ ሃሳብ ሁለት

የደስታ መንደር ተራድኦ ሕብረት (ለምሳሌ የተቀረበ ስም ነው) በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን በተለይም በሴቶች እህቶቻችን መሪነት ከላይ ለምሳሌ በተጠቀሰው መልክ በደስታ መንደር የሚገኙትን ኢትዮጵያዊ እህቶቻችንን ለመርዳት የሚንቀሳቀሱ የእርዳታ ማህበራትን በየምንገኝበት አካባቢ ብናቋቁም ለውጥ ማምጣት እንችላለን።

በምናቋቁማቸው የተራዶ ማህበራት አማካኝነት ጫና በማይፈጥርና ከአቅም በላይ በማይሄድ መልክ በአመት አንዴ ወይም ሁለቴ በመገናኘት ልብሶችን፤ የስፌት መኪናዎችን ታይፐ ራይተሮችን፤ የሹራብ መስሪያዎችንና የመሳሰሉትን መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በማሰባሰብ በቋሚነት ለደስታ መንደር ነዋሪዎች የመላክ ተግባራትን በቀላሉ ማከናወን እንችላለን።

የዚህ ዓላማ ግንባር ቀደም አደራጆች፤ መሪዎችና፤ አሰባሳቢዎች በየሃገሪቱ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እህቶቻችን ቢሆኑ ለተግባራዊነቱና ለውጤቱማነቱ አስተማማኝ ይሆናል የሚል የሚል ዕምነት አለን።

እንግዲህ ዋናው ሃሳቡ ሃሳባችን መሆኑን ከተስማማን ከላይ የቀረቡት ሁለት ንድፈ ሃሳቦች በመነሻነት የቀረቡ እንደመሆናቸው ከምንገኝበት ሃገርና የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ጋር የሚሄዱ የተሻለ ውጤት አምጭ ዘዴዎች ካሉም ተመካክረን፤ ተቻችለን፤ በጽናት ለተግባራዊነቱ እንተጋ ዘንድ ያብቃን!

በመጨረሻም ይህን የተሰፋ ታሪክ ያነበባችሁ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን፤ ላላነበበው አስነብባችሁ የቀረቡትን ንድፈ ሃሳቦችም በቀናነት በመመልከት ትኩረት ትሰጧዋቸው ዘንድ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ከአክብሮት ጋር ይጠይቃል።

በያለንበት ቸር ይግጠመን!

ታህሳህ 2002

መስፍን ማሞ ተሰማ

ሲድኒ አውስትራሊያ።

ጸሃፊውን በዚህ msfntessema@yahoo.com.au ኢሜል አድራሻ ማግኘት ይቻላል።

**ዋቢ መጽሃፍት መጽሃፍት**
1-A story of hope- the hospital by the river By Dr. Cathrine
2-Cathrine's Gift-By Jhon Little

**በአለም ዙሪያ የፊስቱላ ፋውንዴሽን አድራሻዎች**
Australia
Cathrine Fistula Relief and AID Fund
P.o.Box 965
wahroonga N.S.W 2076
fistulaltd@ozmail.com.au

**ENGLAND**
The Hamlin churchill chilbirth injuries Fund
5 victoria avenue
Halesowen
west Midlands
B629BL
UK
hccif@aol.com

**Ethiopia**
The hamlin Festula Welfare and research trust
P.O.Box 3609
Addis Ababa
Ethiopia
fitsula-hospital@telecom.net.et

Bank A/c
The hamlin Festula Welfare and research trust
commercial Bank of ethiopia
Mahatma Gandhi Branch
P.o.Box 255
addis ababa
Ethiopia

**Sweden**
Stiftelesen Fitsulasjukhuset
P.o.Box 19109
10432 stockholm
sweden

**USA**
Aid for international Medicen(AIM)
rocland Mills
P.o.box 119
Rock land De 19732
USA

American Frindes Foundation for childeren Injuries
Ric hass
4030 Moorpark Ave 105
san Jose
ca 95117
USA
richass@earthlink.net